# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ያላቸውን ትስስር በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2004 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# የአርዕስት ማውጫ


**የአርዕስት ማውጫ ..... I**

**ክፍል አንድ ..... 1**

**መግቢያ ..... 1**

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመሠራረት ..... 2
የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር ..... 3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ..... 4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል ..... 4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ..... 4

**የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ..... 5**

**የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..... 5**

**ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ..... 6**

**የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ..... 6**

**የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት (AUDIT EVALUATIVE CRITERIA) ..... 7**

**የአሠራር ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ..... 7**

**ክፍል ሁለት ..... 9**

**የኦዲት ግኝቶች ..... 9**

በጥናትና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪው መካከል ትስስር እንዲኖር የሚያስችል ፖሊሲ መዘጋጀቱንና መጽደቁን በተመለከተ. 9
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፖለሲ በሚያዘጋጅበት ወቅት ባለድርሻ አካላት ማሳተፉን በተመለከተ ..... 10
ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ የኢንደስትሪ የልማት ዘርፎች ላይ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን በተመለከተ ..... 11
የጥናትና ምርምር ተቋማት እና የኢንደስትሪ ትስስርን የማጠናከር ተግባር በእቅድ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ ..... 12
ኢንደስትሪዎች ከምርምር ተቋማት የተሰጣቸውን የምርምር ውጤት በሥራ ላይ አውለው ያገኙትን ውጤት ለምርምር ተቋማት የሚያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ፤ ..... 13
በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱት የምርምር ውጤቶች ያስገኙት ውጤት የሚገመገምበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ ..... 14
ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እንዲሰሩ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ ..... 16
ኢንደስትሪውን ለመደገፍ የተሻሉ የምርምር ሥራዎችን ለሚሰሩ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ማበረታቻ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ ..... 18
የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶች መቋቋማቸውን በተመለከተ ..... 18
በጥናትና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪ ትስስር ዙሪያ ባለድርሻ በሆኑ አካላት የሥራ ክንውን ላይ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ ..... 19
የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር በቅንጅት እንዲከናወኑ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በተመለከተ ..... 20
የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት መደራጀትን በተመለከተ፣ ..... 22
በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎች መረጃ መመዝገብን በተመለከተ ..... 23

**ክፍል ሶስት ..... 25**

**መደምደሚያ ..... 25**

**ክፍል አራት ..... 26**

**የማሻሻያ ሀሳብ ..... 26**

**አባሪዎች ..... I**

መመዘኛ መስፈርቶች (EVALUATIVE CRITERIA) ..... I
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለጥናት ስራ የለያቸው አካባቢዎች ..... III

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለአንድ አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት መፋጠን ያላቸው አስተዋፅኦ ወሳኝ በመሆኑ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እና በተቀናጀ መልኩ እንዲከናወኑ እና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለጥናትና ምርምር ሥራዎች መጀመር እና መስፋፋት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መቋቋም እና መስፋፋት አስተዋጽኦ የጎላ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከነበረው ጋር በንጽጽር ሲታይ የጥናት እና ምርምር ተግባራትን ትኩረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት እና የጥናትና ምርምር ተግባራት እየተስፋፉ የመጡት በቅርብ አስርት ዓመታት ነው፡፡ የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በ1950 ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ስም የተመሠረተ ሲሆን፣ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት መንግስት በያዘው የከፍተኛ ትምህርት ማስፋፋት መርሐ ግብር መሠረት 31 የመንግስት እንዲሁም ወደ 50 የሚጠጉ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋቁመው በተለያየ የትምህርት ዘርፍ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

2. የጥናትና ምርምር ተግባራትን በብቃት ለማከናወን የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር 1979 ጀምሮ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብሮችን የማከናወን እንቅስቃሴ የተጀመረ ሲሆን፣ ባለፈው አስር አመታት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ የቀጠለበት ሁኔታ ይታያል፡፡ እነዚህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በጥራት፣ በጥልቀትና በስፋት ማካሄድ እንዲችሉ የሚሰጡት አገልግሎት ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት በተለይም ከኢንደስትሪው ጋር በተቀናጀ ሁኔታ መከናወን ይኖርበታል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚከናወኑት የጥናትና ምርምር ተግባራት በተጨማሪ በተለያዩ ሴክተሮች እራሳቸውን የቻሉ የጥናት እና ምርምር ተግባርን የሚያከናውኑ ተቋማትም እየተቋቋሙ የተለያዩ የምርምር ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

3. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሆነ ከሌሎች የምርምር ተቋማት የሚወጡ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በየደረጃው ከምርምር ርዕስ መረጣ ጀምሮ ከኢንደስትሪው ጋር በቅንጅት የሚሠሩበት ሁኔታ መፈጠሩ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚችሉ መፍትሄዎችን በማፍለቅ በሀገር ደረጃ ሲታይ

የሚችል ለውጥ ለማምጣት የጎላ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡ በግብርና እና በጤና ዘርፎች የጥናት እና ምርምር ተግባራት የሚካሄዱት በአብዛኛው ራሳቸውን ችለው በየሴክተሮቹ በተቋቋሙ የምርምር ተቋማት ሲሆን፣ በእነዚህም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን እና ወደ ተግባር በመተርጎም ውጤት ለማስገኘት በባለድርሻ አካላት መካከል ተቀናጅቶ መሥራት ወሳኝ ነው፡፡ የሀገሪቱን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የማስተባባር እና የጥናትና ምርምር ሥራዎች በቅንጅት የሚከናወኑበትን ሁኔታ የማመቻቸት ተግባር ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥቷል፡፡ ይህም ሚኒስቴር መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 603/2001 ላይ ተገልጿል፡፡

## የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመሠራረት

4. የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ተግባራትን የሚያስተባብር አካል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1968 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 62/1968 በቀጣይም ከመጀመሪያው የብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ መጽደቅ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 91/86 እንደገና በኮሚሽን ደረጃ እንዲዋቀር ተደረገ፡፡ ከዚያም ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ምሥረታ በኋላ በ1997 ዓ/ም መጠሪያው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ እንዲሆን ተደርጎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም 2001 ዓ.ም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 603/2001 የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴዎችን መደገፍ፣ መምራት፣ ማበረታታትና ማጎልበትን ዋና ዓላማ በማድረግ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

5. የጥናት እና ምርምር ተቋማትም ሆነ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከኢንደስትሪው ጋር በቅንጅት የሚሠሩበትን ሁኔታ እንዲያመቻች በአዋጅ ቁጥር 603/2001 ኃላፊነት በዋናነት የተሰጠው ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ቢሆንም ሌሎች ባለድርሻ የሴክተር መ/ቤቶችም (ኢንደስትሪ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር ወዘተ) የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና የምርምር ስራዎችን በማከናወን ረገድ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

## የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

6. በአዋጅ ቁጥር 603/2001 ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ✓ የሀገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ በመንግስት ሲፀድቁም ተግባራዊ እንዲደረጉ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤
- ✓ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፤ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፤ ለመምረጥ፤ ለማስገባት፤ ለመቀመር፤ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
- ✓ በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፤ የቴክኖሎጂውን ዝርዝር አሠራር መግለፅና (ኮዲፋይድ የማድረግ) የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ለቀጣዩ ሥራ እንቅስቃሴም እንዲውሉ ያደርጋል፤
- ✓ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮገራሞችን ያስተባብራል፣ የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
- ✓ የሳይንስ፤ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን አመላካቾችንም ያዘጋጃል፣ ለአገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፣
- ✓ በመንግስትና በግል የከፍተኛ ትምህርት የምርምር ተቋማትና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስ በእርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- ✓ የሀገሪቱን የረጅም ጊዜ የሣይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የሰው ኃይል ልማት ያቅዳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ከሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤
- ✓ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም የሚገነባበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ✓ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች እድገት አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤
- ✓ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ያቋቁማል፤ ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤

- ✓ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ መዳበር አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሙያ ማህበራትንና አካዳሚዎችን ያበረታታል፤

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር

7. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ በአንድ ሚኒስትርና በአንድ ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ሲሆን፣ በሚኒስትሩ ስር ዘጠኝ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች፣ በሚኒስቴር ዴኤታው ስር ደግሞ አራት ወሳኝ የሥራ ሂደቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዋነኛ የሥራ ሂደቶች የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዳይሬክቶሬት፣ የአቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት፣ የፖሊሲ ምርምር፣ ዝግጅትና ትግበራ ዳይሬክቶሬት እና የእቅድ ዝግጅትና ትግበራ ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡ ከአራቱ ዋና የስራ ሂደቶች አንዱ በሆነው በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዳይሬክቶሬት ስር በሀገራዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች ዙሪያ ዘጠኝ ቨርቹዋል ቡድኖች ተደራጅተዋል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ 181 ቋሚ ሠራተኞች ሲኖሩት የነዚህ ሠራተኞች የትምህርት ሁኔታ ሲተነተን ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው 18 (9.9%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 80 (44.2)፣ ዲፕሎማ ያላቸው 20 (11.05)፣ ሰርትፍኬት ያለው 1 (0.06) ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 62 (34.25) ሠራተኞች ከተገለጹት በታች የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

9. በሀገሪቱ በሚገኙ የምርምር ተቋማት ለጥናት እና ምርምር ተግባር የሚውለው የገንዘብ መጠን በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ቢገመትም ይህን ለማሳየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ባለመቻሉ በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለማካተት አልተቻለም፡፡ ሆኖም የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራውን የሚያካሂደው ከመንግስት በሚመደብለት መደበኛ በጀት እና ከእርዳታ ከሚያገኘው ገቢ ነው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2001፣ 2002 እና 2003 በጀት አመታት ብር 2.18፣ 0.38 እና 0.25 ሚሊየን ከእርዳታ ያገኘ ሲሆን፣ በነዚሁ ተከታታይ የበጀት ዓመታት በመደበኛ በጀት ብር 10.8፣ 17.0 እና 18.6 ሚሊየን ብር ተመድቦለት ከዚህ ውስጥ እንደ ቅደም ተከተሉ 9.3፣

13.8 እና 17.5 ሚሊየን ብር ሥራ ላይ አውሏል፡፡ እንዲሁም በካፒታል በጀት እንደ ቅደም ተከተሉ 1.5፣ 1.4 እና 0.93 ሚሊየን ብር ተመድቦለት ብር 0.92፣ 0.49 እና 0.32 ሚሊየን ሥራ ላይ ያዋለ መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

11.ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል የታየው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከላይ በተጠቀሱት ተከታታይ ዓመታት እንደ ቅደም ተከተሉ ከመደበኛ በጀት 1.2፣ 2.07 እና 2.66 ሚሊየን ብር ለሚያከናውነው የምርምር ተግባር ተመድቦለት ከዚህ ውስጥ እንደ ቅደም ተከተሉ 1.09፣ 1.68 እና 1.05 ሚሊየን ሥራ ላይ ማዋሉን ካገኘነው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

12.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት እና በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚከናወኑ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እና የኢንደስትሪውን ዘርፍ መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ እንዲሆኑ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን በማመቻቸቱ ረገድ እገዛ የሚያደርግና የሚከታተል መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚያግዙ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

# የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

13.የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2001 እስከ 2003 ዓ/ም ባሉ በጀት ዓመታት ውስጥ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ትስስር እንዲኖራቸው ለማስቻል የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኝነት የተከናወነው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን፣ ከተወሰኑ ዋነኛ ባለድርሻ አካላት ማለትም ኢንደስትሪ ሚኒስቴር፤ በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፤ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ከኢንደስትሪዎች መካከል የቆዳ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና የብረታ ብረት ኢንደስትሪ የምርምር ኢኒስቲትዩቶች እንዲሁም የአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ኤጀንሲ እና የጤና እና ስነምግብ ኢኒስቲትዩት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የማሰባሰብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

14.የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ባላቸው ትስስር ዙሪያ ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን ማለትም የሚኒስቴር መ/ቤቱን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት

ለውጥ ጥናት፣ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ከ2001 እስከ 2003 ዓ/ም ያሉ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም የተለያዩ ተያያዥ ጥናቶችን እና የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲን እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ ከላይ ከተጠቀሱ ባለድርሻ አካላት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመከለስ፤ ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ላይ ለሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት እና  የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

15.ለዝርዝር ኢዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ "በከፍተኛ ትምህርት እና በምርምር ተቋማት የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ትስስር ያላቸው መሆኑን እና የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ መፍትሄዎችን በብቃትና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ እየፈጠሩ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው።

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

16.ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ስር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተቀምጠዋል። እነርሱም፥

i. በተለያዩ የጥናት እና ምርምር ተቋማት የሀገሪቱን ዕድገት ለማፋጠን ቅድሚያ በተሰጣቸው ሴክተሮች ላይ የሚከናወኑ የጥናት እና የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ትስስር እንዲኖራቸው የማድረጉ ተግባር ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል  የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ እና ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን መገምገም

ii. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን ዕድገት ለማፋጠን ቅድሚያ በተሰጣቸው ሴክተሮች ላይ በተለያዩ የጥናት እና ምርምር ተቋማት የሚከናወኑ የጥናት እና የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ትስስር እንዲኖራቸው እና ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻች፣ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን መገምገም

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

17.የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 16 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የሚኒስቴር መ/ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ረቂቅ ፖሊሲ እንዲሁም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ከድረ-ገፆች የተገኙ ተያያዥ የሆኑ ጥናቶች በመከለስ እና መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱም በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጥባቸው በማድረግ የዝርዝር ኦዲቱ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የአሠራር ሂደት መግለጫ (Process Description)

18.የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት እና የሳይናስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዋና የሥራ ሂደቶች የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ያላቸውን ትስስር በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር እንዲያከናውኑ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መዋቅር ውስጥ የተደራጁ ናቸው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዋና የሥራ ሂደት የመንግስት ፈጣን የዕድገት ፍላጎትን መነሻ በማድረግ በሀገሪቱ ትኩረት በተሰጣቸው ፕሮግራሞች ዙሪያ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በተገኘው የቴክኖሎጂ ፍላጎት ውጤት ላይ በመመርኮዝ፤

- አግባብነት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎች የማፈላለግ፣ የመለየት፣ ግዥና ምዝገባ እንዲካሄድ የማስተባበርን
- የተመዘገቡ ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ ተቋማት ዲዛይን እንዲደረጉ እና
- የመቅዳትና የማሻሻል ተግባራት እንዲከናወኑ

የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የቴክኖሎጂ ፍተሻ ከተደረገም በኂላም የተረጋገጠውን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እንዲውል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያስተባብራል፡፡ በመጨረሻም የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ በማድረግ ሀገሪቱ ቴክኖሎጂ የማመንጨት አቅም እንዲኖራት በማድረጉ ሂደት ላይ ሰፊ ሚና ይጫወታል፡፡

19.በሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዋና የስራ ሂደት ውስጥ ሶስት የስራ ሂደት ቡድኖች ማለትም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ ቡድን፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓት አቅም ግንባታ ቡድን እና የሳይንስና

ቴክኖሎጂ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ቡድን የተደራጀ ሲሆን፣ ይህ ዋና የሥራ ሂደት የዩኒቨርስቲ ኢንደስትሪን ትስስርን ከማጠናከር ተግባር በተጨማሪ፣

- የምርምር ተቋማትን ማጠናከር እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ማቋቋም፤
- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዙሪያ ለሚሠሩ የሙያ ማህበራትና የፈጠራ ሳይንስ ክበባት ድጋፍ ማድረግ፤
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች የኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲሆኑ ማገዝ እና
- ሥርዓተ ትምህርት ከሳይንስ እና ቴክኖሎጂ አንፃር መቃኘት

እና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችንም ያከናውናል።

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### በጥናትና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪው መካከል ትስስር እንዲኖር የሚያስችል ፖሊሲ መዘጋጀቱንና መጽደቁን በተመለከተ

20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን በዩኒቨርሲቲዎች፣ በምርምር ተቋማትና በኢንደስትሪው መካከል ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ በማዘጋጀት እና በማጸደቅ ለተግባራዊነቱ የሚረዱ መመሪያዎች እና ደንቦችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

21. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በ2001 ዓ/ም በሚኒስቴር ደረጃ ከተቋቋመ በኋላ ያዘጋጀው የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ረቂቅ ፖሊሲ ከያዛቸው 12 ወሳኝ ጉዳዮች መካከል የዩኒቨርስቲዎች፣ የመንግስት የምርምር ተቋማትና የኢንደስትሪ ትስስር አንዱ መሆኑን እና ይህ ረቂቅ ፖሊሲ እንዲፀድቅ ነሐሴ 10 ቀን 2002 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መላኩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ የማስፈፀሚያ ህጋዊ ማዕቀፍ እና ማስፈፀሚያ ደንብ ማዘጋጀትና ማስፀደቅ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመታት ቢታቀድም ተግባራዊ እንዳልሆነ በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

22. ሁኔታውን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፖሊሲው ሳይፀድቅ ከአንድ ዓመት በላይ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እንደቆየ፤ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ህዳር 2 ቀን 2003 ዓ/ም በድጋሚ በተፃፈ ደብዳቤ መ/ቤቱ መጠየቁን፤ ህዳር 8 ቀን 2004 ዓ.ም ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት ቀርቦ አስተያየት የተሰጠበት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ከተስተካከለ በኋላ በድጋሚ እንዲጸድቅ የሚቀርብ መሆኑ ተገልጿል፡፡

23. በተጨማሪም ፖሊሲውን ለመተግባር ደንብ ሳይሆን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ እንደሚዘጋጅ፤ መመሪያው ባይኖርም በአሁኑ ወቅት በጥናትና ምርምር እና

በኢንደስትሪ መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ለመፍጠር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም እንደ መርህ መገልገል እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡

24.የፖሊሲው አለመጽደቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንደስትሪ፣ በዩኒቨርስቲና በሌሎች የምርምር ተቋማት ትስስር ዙሪያ ያዘጋጃቸው ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ እና በዚህ ዙሪያ የታቀዱ ሥራዎችን በአግባቡ ለመፈፀም እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር እንዳይቻል አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፖለሲ በሚያዘጋጅበት ወቅት ባለድርሻ አካላት ማሳተፉን በተመለከተ

25.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖለሲ በሚያዘጋጅበት ወቅት ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

26. “Building competitiveness through Innovation” ሀገር አቀፍ ወርክ ሾፕ 120 ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ላይ ለማወያየት አስቦ 50 ተሳታፊዎች ብቻ በፖሊሲው ውስጥ በተቀመጡ ሀሳቦች ላይ ተወያይተው የተለያዩ አስተያቶችን መስጠታቸውን፤ በ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲን በማስፀደቅ ፖሊሲውን በስፋት ማስተዋወቅ በሚል ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ፖሊሲውን የማስፀደቅም ሆነ የማስተዋወቁ ሥራ ያልተፈፀመና አፈፃፀሙም 35 በመቶ ብቻ በመሆኑ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27.የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የተለያዩ ሀገራት ባለሙያዎችን ለማሳተፍ ጥረት መደረጉን፤ በቁጥር ደረጃ ሳይሆን በተዋጽኦ ደረጃ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በሚወክል ሁኔታ ውይይት የተደረገበት መሆኑን እና ፖሊሲውን የማስተዋወቅ ዕቅድ ቢያዝም ፖሊሲው በታሰበው ወቅት ሊጸድቅ ባለመቻሉ ተግባራዊ አለመደረጉን ሆኖም ህዳር 8 ቀን 2004 ዓ/ም ሚኒስትሮች ምክር ቤት በረቂቅ ፖሊሲው ላይ የተሰጠውን ግብዓት በውይይት አዳብሮ ለማካተት እንዲቻል ሁሉንም ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

28.በፖሊሲው ዝግጅት ወቅት በቂ ቁጥር ያላቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ስለማድረጋቸው የሚገልጽ መረጃ ያልቀረበ ሲሆን፣ ሁኔታው ፖሊሲው የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሀሳብ በማካተት እንዳይዳብር የሚያደርግ እንዲሁም

በወቅቱ ሊጸድቅ ባለመቻሉ ፖሊሲውን የማስተዋወቅ ተግባር መጓተቱ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በወቅቱ ተገንዝበው በጥናትና ምርምር እና በኢንደስትሪው ትስስር ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ቶሎ መፍትሄ ለመስጠት እንዳይቻል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በፖሊሲው ትግበራ ወቅት በባለድርሻ አካላት መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር መንገድ ይከፍታል፡፡

## ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ የኢንደስትሪ የልማት ዘርፎች ላይ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን በተመለከተ

29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንደስትሪውን ችግር ለመረዳት ቅድሚያ በተሰጣቸው የኢንደስትሪ ልማት ዘርፎች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ቅድሚያ የትኩረት አቅጣጫዎች ብሎ ከመረጣቸው ዘጠኙ ዘርፎች ውስጥ በሶስቱ ላይ ማለትም በቆዳ፣ በጨርቃ ጨርቅ እና በብረታ ብረት ኢንደስትሪዎች ላይ ጥናት እንደተደረገ ከቀረቡ መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን (አባሪ 2)፣ ይህን ሁኔታ አስመልክቶ የባለድርሻ አካላትን ለማነጋገር ተሞክሮ የተወሰኑት ማለትም ቆዳ፣ ጨርቃ ጨርቅ እና ብረታ ብረት ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቶች እንዲሁም ጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሀገሪቱ ያሉ የኢንደስትሪ ችግሮችን በማጥናት ለምርምር ተቋማት ማቅረብ እንዳለበት እንደሚያምኑ እና እስከሚያውቁት ድረስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን የዳሰሳ ጥናት በማከናወን ለምርምር ተቋማት አሳውቆ እንደማያውቅ ገልጸዋል፡፡

31. በጨርቃ ጨርቅ ኢንደስትሪው ዙሪያ ያለውን ፍላጎት በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጣ ባለሙያ ኢንደስትሪው ባቀረበው የጥናት ፕሮፖዛል መሠረት መረጃ ለመሰብሰብ የሞከረ ቢሆንም ቀጣይ በሆነ ሁኔታ እንዳልተሄደበት እና በጥቅሉ በምርምር ተቋማትና በኢንደስትሪው መካከል ያለውን ግንኙነት የማጠናከር ተግባር ገና በጅምር ላይ እንዳለ የጨርቃ ጨርቅ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

32. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሀገሪቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሠረት ከነዚህ የዳሰሳ ጥናት የተደረገባቸው የቆዳም ሆነ የጨርቃጨርቅ ኢንደስትሪዎች የግብርናውን ውጤት እንደግብአት ስለሚጠቀሙ ለግብርናው ዘርፍ ማደግ ካላቸው አስተዋጽኦ አንጻር፤

የብረታብረት ኢንደስትሪን ጨምሮ ከሶስቱ ዘርፎች የሚገኘው ጥቅም ከፍተኛ በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት እንደተሰጣቸው፤ በቀጣይም የደሰሳ ጥናት ባልተደረገባቸው ስድስት ዘርፎች ላይ በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት ጥናት እንደሚከናወኑ እና በ2004 ዓ.ም እንደሚጠናቀቁ አስረድተዋል፡፡

33.የመንግስት ቅድሚያ የልማት የትኩረት አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ እና አቅም በፈቀደ መጠን ቅድሚያ በመስጠት በሀገሪቱ የሚገኙ ኢንደስትሪዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ችግሮችን የመለየት እና የማሳወቅ ተግባር መከናወኑ ተገቢ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ከተሰበሰቡ መረጃዎች ይህን አካሄድ በተመለከተ በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ግንዛቤ እንዲኖር የማድረግ ተግባር እንዳልተከናወነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሆኑም በባለድርሻ አካላት በኩል ተገቢው ግንዛቤ ባለመፈጠሩ ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ የኢንደስትሪ የልማት ዘርፎች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረጉ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ተግባር እንዳያከናውኑ ያደርጋል፡፡

## የጥናትና ምርምር ተቋማት እና የኢንደስትሪ ትስስርን የማጠናከር ተግባር በእቅድ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ

34.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥናትና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪ ትስስር ዙሪያ ውጤታማ ተግባራት እንዲከናወን የሚያግዝ ተግባር ለማከናወን እቅድ ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

35.በሚኒስቴር መ/ቤቱ በዩኒቨርስቲ፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪ ትስስር ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ እቅድ ቢያቅድም አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2003 ዓ/ም እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው 940 ለሚሆኑ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተማሪዎች በኢንደስትሪ ውስጥ ስልጠና ለመስጠት የተያዘው እቅድ 120 የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማለትም 12.8 በመቶው ብቻ በተለያዩ ፋብሪካዎች የተግባር ጉብኝት ማድረጋቸው፤ እንዲሁም ለ40 የኢንደስትሪ ሠራተኞች የተግባርና ንድፈ ሀሳብ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ በበጀት ዓመቱ የታቀደ ቢሆንም ክንውኑ ከ50% በታች እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

36.ሁኔታውን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ በበጀት ያልተደገፈ ስለነበር ከአጋሮች

ፈንድ በማፈላለግ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም የሚጠበቀው ድጋፍ በወቅቱ ሊገኝ ባለመቻሉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

37. በበጀት ዓመቱ በኢንደስትሪና በዩኒቨርሲቲ ትብብር ዙሪያ የተሠራው የማጠናከር ሥራ ከእቅዱ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑ ተቋማቱ በጋራ ማከናወን ያለባቸውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችላቸው ልምድ እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ በመካከላቸው ሊኖር የሚገባው የትብብር ግንኙነት እንዳያድግ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## ኢንደስትሪዎች ከምርምር ተቋማት የተሰጣቸውን የምርምር ውጤት በሥራ ላይ አውለው ያገኙትን ውጤት ለምርምር ተቋማት የሚያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ፤

38. ኢንደስትሪዎች ከምርምር ተቋማት የተሰጣቸውን የምርምር ውጤቶች ተቀብለው ሥራ ላይ በማዋል ያገኙትን ውጤት ለምርምር ተቋማቱ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

39. በግለሰብ ደረጃ የማማከር ሥራ የሚሠራ ካልሆነ በስተቀር ከኢንደስትሪው ጋር ያለው ግንኙነት የላላ እንደሆነ እና ለኢንደስትሪው የሰጠውን የምርምር ሥራ ውጤታማነትን የሚገመግምበት ወጥ የሆነ አሠራር የሌለ መሆኑን በናሙና በመምረጥ ካየናቸው የምርምር ተቋማት መካከል አንዱ ከሆነው የጤናና ስነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

40. በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዕፅዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ምክትል ዳይሬክተር ብዙም ችግር ፈቺ የሆነ የምርምር ሥራ ተካሂዷል ማለት እንደማይቻል የገለጹ ሲሆን፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር የስራ ሂደት ዳይሬክተር ደግሞ የምርምር ተቋሙ ከኢንደስትሪው ጋር ግንኙነት የሚያደርገው ቀጥታ በራሱ በኩል እንደሆነና በዚህም ከአሰላ ብቅል፣ ከቢራ እና ከጥጥ ፋብሪካዎች ጋር የተለያዩ ሥራዎችን የሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚሁ ኢንስቲትዩት የእንስሳት ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሳይንስ ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ድጋፍ በመስጠቱ ላይ ብዙ ተሳትፎ እንደማያደርግ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው እራሱ ኢንስቲትዩቱ ወደ ኢንደስትሪው (ከቆዳ እና ከወተት ኢንደስትሪዎች እና ከመሳሰሉት ጋር) በመውረድ በጋራ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መሥራቱን አስረድተዋል፡፡

41.በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት የምርምር ተቋማትና በኢንደስትሪዎች መካከል የተጠናከረ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል የሚል ሲሆን፣ አንዳንድ የጥናትና ምርምር ተቋማት በሀገሪቱ በሚገኙ ኢንደስትሪዎች ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን በራሳቸው ጥረት በመመርመርና በመለየት ጥናት በማድረግ የደረሱባቸውን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራ ውጤቶችን ለኢንደስትሪዎቹ ለማቅረብ የሚሞክሩ ቢሆንም እነዚህን የጥናት እና ምርምር ውጤቶች የተቀበሉ ኢንደስትሪዎች ግን ተግባራዊ አድርገው የደረሱበትን ሁኔታ ለጥናት እና ምርምር ተቋማቱ የሚያሳውቁበት ሁኔታ የለም፡፡

42.ይህንን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በመመዘኛ መስፈርት ላይ በሰጡት አስተያየት ይህ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ጨምሮ በተቋማቱ መካከል የመግባቢያ ሰነድ በሚፈራረሙበት ወቅት የሥምምነቱ አካል ሆኖ የሚዘጋጅ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

43.የጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ውጤቶቻቸው ወደ ኢንደስትሪው ገብተውና በሥራ ላይ ውለው ያስገኙትን ውጤት ምላሽ ከኢንደስትሪዎቹ ባለማግኘታቸው የሥራ ውጤቶቻቸው ለኢንደስትሪው ያስገኙትን ጥቅም ለማወቅ እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው ሲሆን፣ ለወደፊት የምርምር ሥራዎቻቸው በምን አካባቢዎች ላይ ሊያተኩሩ እንደሚገባ ለመወሰን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱት የምርምር ውጤቶች ያስገኙት ውጤት የሚገመገምበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ

44.በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች ለኢንደስትሪው አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸው የሚገመግምበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡

45.በተመለከትናቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሶስት በጀት ዓመታት ማለትም 2001፣ 2002 እና 2003 ሥራዎች እና ዕቅዶች ውስጥ በጥናት እና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የኢንደስትሪውን ችግሮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ስለመሆናቸው፤ የምርምር ሥራ ውጤቶች ለኢንደስትሪው ድጋፍ ለማድረግ ስለመቻላቸው ወዘተ... በተመለከተ የሚገመገምበት ሥርዓት እንደሌለ

እና ይህንን በተመለከተ የሚሠራ ሥራ በእቅድም እንዳልተያዘ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

46. በማዕድን፣ ውሃ፣ ኢነርጂና ጂኦ-ኢንፎርማሽን ሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች የሚካሄዱት አብዛኛዎቹ የምርምርና ስርፀት ተግባራት ከመንግስት በሚገኙ ድጋፎች በአዲስ አበባ፣ በባህርዳርና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲዎች ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች እና በተወሰኑ የመንግስት መ/ቤቶች የሚካሄዱ ሲሆን፣ እነዚህ እንቅስቃሴዎች የምርምር ልምድና ባህልን ከመገንባትና የመማርና ማስተማር ሂደቱን ከመደገፍ ያለፈ ፋይዳ አስገኝተዋል ማለት እንደማይቻል የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ላይ ተገልጿል፡፡

47. የኢንደስትሪ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እስካሁን ባለው ሁኔታ የምርምር ተቋማት የሚያከናውኗቸው የምርምር ሥራዎች በኢንደስትሪው ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን በሚፈታ መልኩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ ክትትል እና ድጋፍ እንደሌለ፤ እንዲሁም የኢንደስትሪውን ችግርን የሚፈታ ምርምር ሥራ ተሠርቷል ለማለት እንደማይቻል የገለጹ ሲሆን፣ የኢንደስትሪውን ዘርፍ ለማገዝ የሚያስችል ተግባር ባሉት የጥናት እና ምርምር ተቋማት በተፈለገው ደረጃ እየተከናወነ ባለመሆኑ ኢንደስትሪዎቹ በራሳቸው የምርምር ሥራ በመሥራት ራሳቸውን እንዲያግዙ መንግስት የቆዳ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና የብረታ ብረት ኢንስቲትዩቶች እንዲቋቋሙ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

48. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁኔታውን አስመልክቶ በቀረበለት የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ባልጸደቀ ፖሊሲ የተቀመጡ እስትራቴጂዎች እንዳልተፈጸሙ ተደርጎ መነሳት እንደሌለበት ሆኖም መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ኃላፊነት ውስጥ የተካተተ በመሆኑ እስካሁን ሲታይ የነበረውን ክፍተት ግንዛቤ ውስጥ በመክተት የምርምር ተግባራት ከኢንደስትሪው ተጨባጭ ሁኔታ እንዲነሱ ለማስቻል የደሰሳ ጥናት እያከናወነ መሆኑን እንዲሁም ፖሊሲው ሲጸድቅ የሚቋቋመመው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት ቅንጅታዊ አሠራሩ እንዲጠናከር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል በሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡

49.ለመግለጽ የተሞከረው የፖሊሲውን መጽደቅ አለመጽደቅ የሚመለከት ሳይሆን የጥናትና ምርምር ተቋማት ውጤቶች ለኢንደስትሪው ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለማድረጋቸውን ከማረጋገጥ አኳያ እየፈጠረ ያለውን ክፍተት ለማሳየት ነው፡፡ የጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ውጤቶች የኢንደስትሪውን ችግር መሠረት ያደረጉና በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች ለመቅረፍ የሚያግዙ መሆን አለመሆናቸው የሚገመግምበት መንገድ አለመኖሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ውጤታማ ተግባራትን እያከናወኑ መሆን አለመሆናቸውን እና ለዚህ ተግባር የሚመደበው ሀብት ውጤት እያስገኘ መሆኑን ለማወቅ አያስችልም፡፡

## ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እንዲሰሩ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ

50.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንደስትሪውንና ምርምር የሚካሄድባቸውን ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር ለማጠናከር የሚያስችል የአሠራር ሥርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

51.በኢንደስትሪው እና በጥናትና ምርምር ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ለመፍጠር የሚያስችል የአሠራር ሥርአት መዘርጋቱን በተመለከተ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት መረጃ ለማሰባሰብ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የእንስሳት ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ወርክሾፖችና ስብሰባዎች ላይ በጋራ ከመሳተፍ የዘለለ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከምርምር ተቋሙ ጋር በጋራ የሚሠራበት ሁኔታ እንደሌለ፤ ይልቁንም ከኢንደስትሪ ሚኒስቴር ጋር የተሻለ የሥራ ግንኙነት እንዳላቸው፤ በአጠቃላይ ሲታይ የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ትስስር እንዲኖራቸው በማድረጉ ረገድ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ የሚታይ አለመሆኑን፤ እንዲሁም የግብርና ምርምር ተቋሙ በራሱ ወደ ኢንደስትሪው በመውረድ ከወተትና ከቆዳ ኢንደስትሪዎች ጋር በጋራ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52.በኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር የሥራ ሂደት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቅንጅት ሥራ ቢሠራ እና በተለይም በግብርና ዙሪያ ሌሎች የምርምር ተቋማት ከግብርና ምርምር ተቋሙ ጋር አብሮ የመሥራት ልምድ ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ ቢያመቻች

ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን እንደሚያስችል ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄ የቀረበላቸው የኢንደስትሪ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች አግሮ ፕሮሰሲንግና ኬሚካልን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሠሩ የሚገቡ ሁኔታዎች ቢኖሩም የአሠራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ የተሠራ ሥራ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

53. የቆዳ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንስቲትዩቱ በቆዳው ዘርፍ ፖሊሲ ከማውጣትና ከማሻሻል ጀምሮ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ክፍተቶችን በመለየት ሊሻሻሉ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ተግባር የማከናወን ኃላፊነት እንዳለበት፣ ኢንስቲትዩቱ በራሱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቀጥታ ግንኙነት የማድረግ ተግባርም እንደሚያከናውን እንዲሁም ይህን ሁኔታ በተሻለ ሁኔታ ተቀናጅቶ እንዲከናወን ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

54. ኢንደስትሪውና የጥናት እና ምርምር ተቋማት ተቀናጅተው እንዲሠሩ የሚያደረግ የአሠራር ስርዓት በሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ረቂቅ ፖሊሲ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተጠናው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውስጥ እንደተካተተ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ ፖሊሲው ባለመጽደቁ ቅንጅታዊ አሠራርን ለማጠናከር በጥናት ደረጃ የተቀመጠውን የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የኢንደስትሪ እና የምርምር ተቋማት ትስስርን በተመለከተ ችግሮችን ለመለየት የመግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ረገድ የተጀመሩ ሥራዎች ቢኖሩም ውጤታማ የሆኑ ተግባራት ለማከናወን እንዳልተቻለ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

55. በፖሊሲው አለመፅደቅና በቅንጅታዊ የአሠራር ሥርዓቱ ተግባራዊ አለመሆን ምክንያት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ቅንጅታዊ አሠራሩን ከማመቻቸት አንጻር ሊጫወት የሚገባውን የማስተባበር ሚና በተገቢው መልኩ እንዳያከናውን፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን አብሮ የመሥራትና የትብብር መንፈስ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሄድ እንዲሁም ባለድርሻ አካላትም የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዳይወጡ እንቅፋት ሆኗል፡፡

## ኢንደስትሪውን ለመደገፍ የተሻሉ የምርምር ሥራዎችን ለሚሰሩ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ማበረታቻ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኢንደስትሪውን ለመደገፍ አቅም ያላቸውና የተሻሉ የምርምር ሥራዎችን ለሚሠሩ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ማበረታቻ ሊሰጥ ይገባል፡፡

57. በናሙና ተለይተው መረጃ ከተሰበሰበባቸው ባለድርሻ አካላት መካከል በብረታ ብረት ልማት ኢንደስትሪ ኢንስቲትዩት የምርትና ዲዛይን ልማት ዳይሬክተር የተሻለ የፈጠራ ሥራ ለሚሠሩ ባለሙያዎች የማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበት ሁኔታ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሌለ እና ሊፈጠር እንደሚገባ የገለፁ ሲሆን፣ የጤናና ስነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ ለኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች ሽልማት የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳልነበር ገልጸዋል፡፡

58. ዩንቨርስቲዎችና የመንግስት  የምርምር ተቋማት ሀገራዊ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ፕሮግራሞች መሠረት አድርገው የሚያከናውኗቸውን የጋራ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የምርምር ተግባራትን ለማበረታታት ልዩ የድጋፍ ፈንድ እንደሚቋቋም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ወደ ተግባር እንዲተረጎም አለመደረጉን ከሚኒስቴሩ የሥራ ኃላፊዎች ገለጻ ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. ዩንቨርስቲዎችና የምርምር ተቋማት ሀገራዊ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ፕሮግራሞች መሠረት አድርገው የሚያከናውኗቸውን የምርምር ሥራዎች ለመደገፍ ተከታታይ እና ቀጣይነት ያለው የማበረታቻ ድጋፍ (ፈንድ) አለመኖሩ እና አለመሰጠቱ ተመራማሪዎች ለሚያከናውኗችው የምርምር ሥራዎች ተነሳሽነታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶች መቋቋማቸውን በተመለከተ

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ሊያቋቁም፣ ሊያስተባብርና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

61.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶች ማቋቋም እንዳለበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም እነዚህ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ አልተደረገም፡፡

62.ብሔራዊ የሳይንስና ቴኬኖሎጂ ምክር ቤቶች የሚቋቋሙበት ዋናው ዓላማ የምርምር ድግግሞሽና የሀብት ብክነትን ለማስቀረት እንደሆነ እና የፖሊሲው አለመጽደቅ ለምክር ቤቱ አለመቋቋም ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ቅንጅታዊ ሂደቱን የሚደግፉ ዘጠኝ ቴክኒካል ቡድኖች የተቋቋሙ መሆኑን፤ በቀጣይም የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እንዲቻል የመግባቢያ ሰነድ የሚፈረም እና የፖሊሲውን መጽደቅ ተከትሎ ምክር ቤቱ ሲቋቋም የተሻለ ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ሁኔታ እንደሚፈጠር ሁኔታውን አስመልክቶ መጠይቅ የቀረበላቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

63.የምርምር ሥራዎችን የሚያስተባብሩ ምክር ቤቶች አለመቋቋም የምርምር ሥራዎችን በባለቤትነት የሚያስተባብር አካል እንዳይኖር እንዲሁም በምርምር ተቋማት መካከል የምርምር ድግግሞሽ እንዲኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## በጥናትና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪ ትስስር ዙሪያ ባለድርሻ በሆኑ አካላት የሥራ ክንውን ላይ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

64.የጥናት እና ምርምር ተቋማት ከመንግስት በጀት እና ከእርዳታ ለምርምር ተግባራት ማከናወኛ የሚያገኙትን ገንዘብ በትክክል ለምርምር ሥራ ማዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችልበትን ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

65.ለምርምር ተቋማት የሚመደበው በጀት በትክክል ለምርምር ሥራ መዋሉን ለመከታተል ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፈንድ እንደሚቋቋም በረቂቅ ፖሊሲ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሁኔታውን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የሥራ ኃላፊዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው ይህ የኢኖቬሽን ፈንድ የምርምር ውጤቶችን ወደ ሥራ ለማሸጋገር እንጂ ለምርምር የሚመደብ በጀት በትክክል ሥራ ላይ ለመዋሉ ክትትል ለማድረግ አለመሆኑን እና ግንኙነት እንደሌለው፤ ፖሊሲው ባልጸደቀበት ሁኔታ የኢኖቬሽን ፈንድ ተግባራዊ አልተደረገም በሚል ሊነሳ እንደማይገባ በሌላ በኩል ደግሞ

ለምርምር የተመደበ በጀት በትክክል ሥራ ላይ ለመዋሉ የመከታተል ተግባር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተሰጠ በመሆኑ ተጠያቂ ሊሆን እንደማይገባ ገልጸዋል፡፡

66.የጥናት እና ምርምር ተቋማት ለሚያከናውኑት የጥናትና ምርምር ሥራ ከተለያዩ ምንጮች የሚመደበው በጀት በትክክል ለምርምር ሥራ መዋሉን ለመከታተል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ መደረጉ ሀገሪቷ ባላት ውስን የኢኮኖሚ አቅም ውጤታማ የጥናት እና ምርምር ተግባራትን ማከናወኗን ለመከታተል እና ብክነትን ለመቀነስ ካለው ጠቀሜታ አንፃር በረቂቅ ፖሊሲው ውስጥ ሊካተት ይገባል የሚል ዕምነት ያለን ሲሆን፣ ይህ የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመሆኑ ለምርምር ሥራ የሚመደበው በጀት በትክክል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል እንዳይቻል ያደርገዋል፡፡

## የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር በቅንጅት እንዲከናወኑ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በተመለከተ

67.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ብቃት ባለው ሁኔታ በቅንጅት እንዲከናወኑ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

68.የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚረዳ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ እንዲውል አልተደረገም፡፡ በናሙና ተለይተው መረጃ ከተሰበሰበባቸው ባለድርሻ አካላት መካከል በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የእንስሳት ጥናት ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር እና የሰብል ምርምር ዳይሬክተር ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ ሪፖርቶችን ከመላላክ ያልዘለለና ሥርዓት ተዘርግቶለት የሚከናወን እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ የኢንደስትሪ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ በኬሚካል ኢንደስትሪ በተወሰነ ደረጃ የመረጃ ልውውጥ ያለ መሆኑን እና በቅርቡም ሚኒስቴሩ የቴክኖሎጂ ፍላጐትን በሚመለከት መጠይቅ እንዳቀረበላቸው ሆኖም የሥራ ግንኙነቱ ሥርዓት ተዘርግቶለት የሚከናወን አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

69.በተጨማሪም በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና የዕፅዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር በግብርና ሚኒስቴር እና በግብርና የምርምር ተቋማት መካከል የተሻለ የመረጃ ልውውጥ ቢኖርም በአጠቃላይ በዚህ ዙሪያ

ባሉ ባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩን የገለጹ ሲሆን፣ የብረታ ብረት ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የምርትና ዲዛይን ልማት ዳይሬክተር ደግሞ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩን እና ወደፊት አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

70. እንዲሁም የቆዳ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለመኖሩ ኢንስቲትዩቱ በግልፅ እንደማያውቅ ነገር ግን ተቋሙ በራሱ መረጃ ለማግኘት ጥረት እንደሚያደርግ እና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠንቶ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ተደርጎ ተግባራዊ ቢደረግ የመረጃ ልውውጡን ውጤታማ እንደሚያደርገው በተለይ በሃገሪቱ የመረጃ ማጠናቀርና ማቅረብን በተመለከተ እየታየ ካለው ክፍተት አንፃር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የገለጹ ሲሆን፣ የጨርቃጨርቅ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ እስካሁን ብዙም የመረጃ ልውውጥ ከኢንስቲትዩቱ ጋር የተደረገበት ሁኔታ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ የጤናና ስነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃዎችን በመፅሄትና በበራሪ ወረቀቶች መልክ እንደሚልክ ነገር ግን ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

71. የሚመለከታቸው የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን በተመለከተ በብሔራዊ ደረጃ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል እንደሚቋቋም በረቂቅ ፖሊሲው ውስጥ መካተቱን፤ በዚህ የመረጃ ማዕከል ለምርምር ተቋማት የሚረዳና የኢንደስትሪውን ችግር የሚፈታ መረጃ ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ ሁኔታ እንደሚያዝ፤ ይህ ማዕከል እንዲቋቋም የሚያግዝ ደንብ የተዘጋጀ እና በቅርብ (በ8/03/2004 ዓ.ም) የጸደቀ ቢሆንም ረቂቀ ፖሊሲው ባለመጽደቁ ተግባራዊ ለማድረግ እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

72. የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራ ከኢንደስትሪው ጋር ያላቸውን ትስስር በተመለከተ መረጃዎችን በቀላሉ

ለመለዋወጥ እና ውጤታማ ተግባራትን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እንዳይሰሩ አድርጓል፡፡

## የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት መደራጀትን በተመለከተ፣

73. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለድርሻ አካላት የምርምር ሥራ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት እና ለመለዋወጥ እንዲችሉ እንዲሁም አላስፈላጊ የምርምር ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲቻል የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት ሊያደራጅ፣ መረጃዎችን ሊያጠናቅርና አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ሊያወጣ ይገባል፡፡

74. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያግዙ የምርምር ሥራ መረጃዎችን ለማጠናቀር የሚረዳ የተደራጀ የመረጃ ቋት የለም፡፡ በናሙና ተለይተው መረጃ ከተሰበሰበባቸው ባለድርሻ አካላት መካከል በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር የሥራ ሂደት ዳይሬክተር ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው መጠይቅ የሀብት ብክነትን ለማስቀረት የምርምር ሥራዎች መረጃዎች ለመጠቀም እና ለመለዋወጥ አመቺ በሆነ ሁኔታ ሊያዙ እና በመናበብ ሊሠሩ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

75. ሁኔታውን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ምላሽ መ/ቤቱ ከተቋቋመ ጀምሮ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ እንደነበርና በ2004 በጀት አመት ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ እንደገባ በዚህም መሰረት የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል የማቋቋሚያ ደንብ ተዘጋጅቶ በሚኒስቴሮች ም/ቤት እንዲፀድቅ የተደረገ መሆኑን፣ በአሁኑ ሰዓት ተቋሙ በአስቸኳይ ወደ ሥራ እንዲገባ የሚያስችሉ ተዛማጅ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ፣ የፖሊሲውን መጽደቅ ተከትሎ አገር አቀፍ የመረጃ ቋት እንደሚቋቋምና በዚሁ በመታገዝ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ይኖራል ተብሎ እንደሚታሰብ፤ እንዲሁም ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት የሚቋቋምበት ዋናው ዓላማ የምርምር ድግግሞሽና የሀብት ብክነትን ለማስቀረት መሆኑን፤ የመረጃ ሥርዓቱ በአሁኑ ጊዜ ተግባራዊ ባለመደረጉ እና ይህንን ተከትሎ መመሪያ ባለመዘጋጀቱ የምርምር ድግግሞሽ

እንዳይከሰት ለመከታተል እንዳይቻል ማድረጉን ይሁን እንጂ የፖሊሲውን መፅደቅ ተከትሎ የመረጃ ማዕከሉ እንደሚቋቋም ገልፀዋል፡፡

76.የመረጃ ማዕከሉ ባለመቋቋሙ በተለያዩ ዘርፎች የሚደረጉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ያለመናበብ እንዲሠሩ እና ከምርምር ሥራ የሚገኘውን ጥቅም ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ለምርምር የሚወጣው ውስን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዳይውል ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

## በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎች መረጃ መመዝገብን በተመለከተ

77.በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎች መረጃ የመመዝገብ፣ ኮዲፋይድ የማድረግና የማቀብ ሥራ መከናወን አለበት፡፡

78.የአዕምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የፈጠራ ሥራዎችን መረጃ ዓለም አቀፋዊ በሆነ ሁኔታ በማረጋገጥ መዝግቦ እንደሚይዝ፣ ከጊዜ በኂላ በህዝብ ሀብትነት የተያዙትን መረጃዎች ለሚጠይቁ የምርምር ተቋማት እና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት እንደሚያስተላልፍ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተመራማሪዎች እና ተመራማሪዎቹ በሚሠሩባቸው ድርጅቶች መካከል የፈጠራ ሥራዎችን በማስመዝገብ ረገድ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መፍትሄ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጠር መሆኑን እና የምርምር ሥራዎችን ማስመዝገብን በተመለከተ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ገና ባለመፅደቁ ቀጣይ ሥራዎችን መሥራት እንዳልተቻለ ከጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ገለጻ እና የሥራውን ሁኔታ በአካል በመመልከት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

79. በተጨማሪም ለሀገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃ ማሰባሰቢያ የሚሆን ዳታ ቤዝ ዝግጅት የመጀመሪያና የሁለተኛው ምዕራፍ ሥራ የተጠናቀቀ ቢሆንም አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ ስላልተከናወነ ወደ ዳታ ቤዙ መረጃ የማስገባት ሥራ አለመሠራቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2002 ዓ/ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት ይህ አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ በረቂቅ ፖሊሲው እንዲመላከት የተደረገ፤ ለሁለት ዩኒቨርስቲዎችና ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከራሳቸው ነባራዊ ሁነየታ ጋር በማገናዘብ

እንዲጠቀሙበት ሞዴል ተቋማዊ የአእምሮአዊ ንብረት ማስተዳደሪያ መመሪያ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸውና ከዚህ ተሞክሮ በመነሳት ሌሎች ተቋማት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ መታሰቡን ሆኖም ይህ ተግባር በተሟላ ሁኔታ የሚከናወነው የመቋቋሚያ ደንቡ በቅርብ በፀደቀለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

80. የጥናት እና ምርምር ውጤቶችን በማስመዝገቡ ረገድ በተመራማሪዎች እና በድርጅቶቻቸው መካከል እየተፈጠረ ያለው አለመግባባት እንዲሁም የሀገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃን የማሰባሰቡ ተግባር አለመከናወኑ የምርምር ሥራዎች መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንዳይቻል እና በወቅቱ ተግባራዊ እንዳይሆኑ የጎላ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

81. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት በጥናት እና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪው ዙሪያ ቅንጅታዊ አሠራር ለማጠናከር የሚያግዙ ተግባራት በረቂቅ ፖሊሲው ውስጥ እንዲካተቱ ማድረጉ እና ጥናት ሊደረግባቸው የሚገቡ አካባቢዎች ተለይተው በተወሰኑ የኢንደስትሪ ዘርፎች ዙሪያ የደሰሳ ጥናት ማከናወኑ የሚበረታታ ተግባር ነው፡፡

82. ሆኖም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ አለመፅደቁ፤ የባለድርሻ አካላት ኃላፊነት በዝርዝር እንዲዘጋጅ አለመደረጉ፤ በሥራ ላይ የዋሉት የምርምር ሥራዎች ያስገኙት ውጤት የሚገመገምበትና በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች የሚመደበው በጀት በትክክል ለምርምር ሥራ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩ እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የመረጃ ማዕከል አለመደራጀቱ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዱ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች እንዳይተገበሩ፤ ባለድርሻ አካላትን በብቃት ለማሳተፍ እንዳይቻል እና የተሻለ የመረጃ ልውውጥ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡

83. ይህም በሀገሪቱ የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች በተሻለ ብቃት እንዳይከናወኑ፤ ለምርምር ሥራ የሚመደበው ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እንዲሁም የተፈተሹ ወቅታዊነትና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የጥናት እና ምርምር ሥራ ውጤቶች ለኢንደስትሪው መሻሻል የተሻለ አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል፡፡

84. ስለሆነም እነዚህን የተጠቀሱን ግድፈቶች ለማቃለል ይረዳሉ ብሎ የኦዲት ቡድኑ ያሰባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል ተገልፀዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ

85. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲው አለመጽደቅ የጥናት እና ምርምር ተቋማት ከኢንደስትሪው ጋር በተቀናጀ ሁኔታ እንዲሠሩ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ያለውን ወሳኝ አስተዋጽኦ እና እስከ አሁን አለመጽደቁ እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለሚመለከተው የበላይ አካል በማሳወቅ ፖሊሲው እንዲፀድቅ እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

86. የጥናት እና ምርምር ተቋማት እና በኢንደስትሪው ቅንጅታዊ አሠራር ዙሪያ ባለድርሻ በሆኑ አካላት መካከል ግልጽ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር እና በተቀናጀ ሁኔታ መሥራት እንዲችሉ የዩኒቨርስቲ፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንደስትሪ ትስስር መመሪያ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

87. የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ረቂቅ ፖሊሲው የሚኒስቴር መ/ቤቱንም ሆነ የባለድርሻ አካላትን የተሟላ አስተያየት አካቶ እንዲዳብርና የተሻለ የሥራ ግንኙነትን በመፍጠር ለመሥራት የሚያስችል እንዲሆን ሊፈተሽ እና እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው እንዲከለስ በማድረግ የባለድርሻ አካላት በቂና ተከታታይ ተሳትፎ እንዲኖር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ በተወሰነ የጊዜ ገደብም ከባለድርሻ አካላቱ ጋር በጋራ በመወያየት በቅንጅታዊ ሥራው ስለተገኘው ለውጥና ስላጋጠሙ ችግሮች በጋራ በመወያየትና የጋራ መፍትሄ ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡

88. የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከመካሄዳቸው በፊት በኢንደስትሪዎች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የሚታዩ ክፍተቶች ተለይተው ለጥናትና ምርምር ተቋማት ግልፅ የሚደርጉበት እና በእነዚህ ተቋማት ለሚከናወኑ የጥናትና ምርምር ተግባራት እንደ ግብአት እንዲያገለግሉ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓትን ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

89. ከዩንቨርሲቲ፣ ከምርምር ተቋማትና ከኢንደስትሪዎች ትስስር ቅንጅታዊ አሠራር ሊገኝ የሚችለውን ሀገራዊ ጥቅም ለማሳደግና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ በዚህ ዙሪያ የታቀደ እቅድና የእቅድ ክንውን

አፈፃፀም በመከታተልና ለአፈፃፀም ብቃት ማነስ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች በመለየት አፈፃፀሙን ለማሳደግ የሚያስችል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

90. የምርምር ተቋማትና የኢንደስትሪዎችን ትስስር በማጠናከር የጥናትና ምርምር ሥራዎች ወደ ኢንደስትሪዎች ገብተው ያስገኙት ፋይዳ ለምርምር ተቋሙ የሚገለፅበት እና በኢንደስትሪዎቹ ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን መሠረት በማድረግ የሚከናወኑ እነዚህ የጥናት እና ምርምር ውጤቶች ለኢንደስትሪው መሻሻል ያስገኙት ጥቅም በየወቅቱ ሊገመግም የሚችልበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

91. የኢንደስትሪውን ችግር ፈቺ እና ተግባር ተኮር የሆኑ ምርምሮች ለማከናወን እንዲቻል በእንደስትሪው እና በጥናትና ምርምር ተቋማት መካከል በተቀናጀ ሁኔታ ለመሥራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

92. የሀገሪቱን ችግር ለሚፈቱና ለእድገትና መሻሻል አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ፣ የምርምር ውጤታቸውን ኢንደስትሪዎች ተግባራዊ አድርገው የተሻለ ውጤታማ እንዲሆኑ ላደረጉ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ማበረታቻ እንዲኖር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

93. የምርምር ሥራዎችን የሚያስተባብሩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምክር ቤቶች ድጋፍ አግኝተው እንዲቋቋሙ እና የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ለሀገሪቱ ኢንደስትሪዎች ውጤታማነት ግብዓት እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተሻለ ሥራ ሊሠሩ እንዲችሉ ጥረት ሊያደረግ ይገባል፡፡

94. የምርምር ሥራ ውጤቶችን በመጠቀም በሀገሪቱ የሚገኙ ኢንደስትሪዎች ውጤታማና የተሻለ እድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማስቻል ለምርምር ተቋማት የምርምር ሥራ ተግባር በመንግስት የሚመደበው በጀትና ከተለያዩ ምንጮች በዕርዳታ የሚገኘው ገንዘብ በትክክል ውጤታማ ሊሆኑ ለሚችሉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች መዋላቸውን ለማረጋገጥና ለመገምገም የሚቻልበት ሁኔታ እንዲፋጠን ሁሉንም የባለ ድርሻ አካላት በማስተባበር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

95. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገር አቀፍ የምርምር መረጃ ማዕከልን ማቋቋሙና የመረጃ ቋት ማደራጀቱ በሀገሪቱ ላይ የሚከናወኑ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን እንዲሁም ከጥናትና ምርምር ተቋማት ወደ ኢንደስትሪዎች የሚሄዱ የጥናትና

ምርምር ሥራ ውጤቶች ለኢንደስትሪዎቹ ዕድገትና መሻሻል ያስገኙት ፋይዳ በማዕከል ለመያዝ፤ የሀገሪቱ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ፤ ቀጣይ የምርምር አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ እና የምርምር ሥራዎችን በወቅታዊ እና በቂ መረጃዎች ለማስደገፍ፤ የምርምር ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲሁም ውስን የሆነውን የተመራማሪዎች ጊዜና ለምርምር የሚወጣውን ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል እገዛ በማድረግ አስተዋጽኦው የጎላ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት ይኖርበታል፡፡

96. በሽግግር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ በአግባቡ የመመዝገብ፣ ኮዲፋይድ የማድረግና የማቀብ ሥራ መሠራቱ መስል ቴክኖሎጂዎች በወቅቱና በተገቢው ሁኔታ ለተፈለገው ዓላማ እንዲውሉ ብሎም የማሻሻያ ሥራዎች እንዲሠሩ ስለሚያርግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እነዚህን መረጃዎች በሚገባ ማደራጀትና መረጃውን ለሚፈልጉ ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪዎች

አባሪ 1

## መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኢንደስትሪውንና ምርምር የሚካሄድባቸውን ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር ለማጠናከር የሚያስችል ሥርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን በዩንቨርሲቲዎች፣ በምርምር ተቋማትና በኢንደስትሪው መካከል ትስስር እንዲኖር የሚያስችል ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብ ሊያዘጋጅ እና እንዲጸድቅ በማድረግ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኢንደስትሪውን ችግር ለመረዳት ቅድሚያ በተሰጣቸው የኢንደስትሪው የልማት ዘርፎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥናትና ምርምር ተቋማት እና ኢንደስትሪ ትስስር ዙሪያ ውጤታማ ተግባራት እንዲከናወን የሚያግዝ ተግባር ለማከናወን እቅድ ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ተቋማት ከመንግስት በጀትና ከእርዳታ የሚያገኙትን ገንዘብ በትክክል ለምርምር ሥራ ማዋላቸውን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
6. በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች ለኢንደስትሪው አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸው የሚገመግምበት መንገድ ሊኖር ይገባል፡
7. ኢንደስትሪዎች ከምርምር ተቋማት የተሰጣቸውን የምርምር ውጤቶች ተቀብለው ሥራ ላይ በማዋል ያገኙትን ውጤት ለምርምር ተቋማቱ ማሳወቅ አለባቸው፡፡
8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንደስትሪውና በምርምር ተቋማት መካከል ችግር ፈቺና ተግባር ተኮር የሆኑ ምርምሮች እንዲያካሂዱ የምርምር ተቋማት አቅም ሊጎለብት የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡
9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኢንደስትሪውን ለመደገፍ አቅም ያላቸውና የተሻሉ የምርምር ሥራዎችን ለሚሠሩ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ማበረታቻ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችን ሊያቋቁም፣ ሊያስተባብርና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
11. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለያዩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ቅንጅት ባለው መልኩ እንዲከናወኑ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
12. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምርምር ተቋማትና ኢንደስትሪው የምርምር ሥራ መረጃዎችን ለመለዋወጥ እና የምርምር ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲቻል

የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት ሊያደራጅ፣ መረጃዎችን ሊያጠናቅርና አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ሊያወጣ ይገባል፡፡

13. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ የመመዝገብ፣ ኮዲፋይድ የማድረግና የማቀብ ሥራ መሥራት አለበት፡፡

14. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖለሲ በሚያዘጋጅበት ወቅት ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይግባል፡፡

15. የጥናትና ምርምር ሥራ ከኢንደስትሪው ጋር ባለው ትስስር ዙሪያ የባለድርሻ አካላት ሃላፊነት በግልፅ መቀመጥ አለበት፡፡

16. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችል ለባለድርሻ አካላት በአዋጅ የተሰጠውን እንዲሁም ባለድርሻዎቹም ያለባቸውን ስልጣንና ሃላፊነት በተመለከተ ለማስተዋወቅ የሚያግዝ ሥራ መሰራት አለበት፡፡

አባሪ 2

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለጥናት ስራ የለያቸው አካባቢዎች

| ተ.ቁ | ዝርዝር | ጥናት የተደረገባቸው | ጥናት ያልተደረገባቸው |
|---|---|---|---|
| 1 | የግብርና ምርታማነት ማሻሻያ ፕሮግራም | | X |
| 2 | የኢንደስትሪ ምርታማነትና ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም፤ | | |
| 1.1 | የምግብ ማምረቻ ቴክኖሎጂ | | X |
| 1.2 | የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ቴክኖሎጂ | √ | |
| 1.3 | የጨርቃ ጨርቅ ቴክኖሎጂ | √ | |
| 1.4 | የስኳር ቴክኖሎጂ | | X |
| 1.5 | የኬሚካልና የመድሃኒቶች ማምረቻ ቴክኖሎጂ | | X |
| 1.6 | የብረታ ብረት ውጤቶች ምህንድስና | √ | |
| 3 | ባዮቴክኖሎጂ | | X |
| 4 | የኢነርጂ ቴክኖሎጂ | | X |
| 5 | የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ | | X |
| 6 | የቁሳቁስ/ማቴሪያልስ/ ቴክኖሎጂ | | X |
| 7 | ኤሌክትሮኒክስና ማይክሮ ኤሌክትሮኒክስ | | X |
| 8 | የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና ቴሌኮሚኒኬሽን | | X |
| 9 | የውሃ ቴክኖሎጂ | | X |